የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 49851

ሚያዝያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት

**ተጠሪ**፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞላ አያት የነበሩት ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባነሽ ደስታ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም ውልና ማስረጃ ቀርበው ሁለት ምስክሮች ባሉበትና በውልና ማስረጃ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፊት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 የቤት ቁጥር 872 የሆነውን መኖሪያ ቤትና ሌሎች ንብረቶች በሙሉ በኑዛዜ መስጠታቸውን በመናዘዝ ህፃን ሮቤል ንጉሤ የኑዛዜ ወራሻቸው መሆኑን በማረጋገጥ ፈርመውበት ምስክሮችም ፈርመውበትና ባለሥልጣኑም ይህንን አረጋግጦ ኑዛዜውን መዝግቦ አንድ ኮፒ አስቀምጧል፡፡ አንድ ኮፒ በኑዛዜ ተጠቃሚ ተሰጥቷል ስለዚህ ህፃን ሮቤል ንጉሤ የሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ ወራሽ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ሁለት ምስክሮች በማስቀረብ ሰምቷል፡፡ ሟች ውልና ማስረጃ ኑዛዜ ማድረጋቸውን መስክሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኑዛዜ ሰነዱንና የምስክር ቃል ከመረመረ በኋላ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን ፎርም አላሟላም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውልና ማስረጃ ባለሥልጣን በምስክርነት ስሙ ያልተጠቀሰና ያልተፈረመ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን መስፈርት አያሟላም፡፡ አመልካች ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስትር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር 044/7/2001 ኑዛዜ ያደረጉ መሆናቸው በክፍሉ ባለሥልጣን ተረጋግጦና ተፈርሞ የተሰጠን ማስረጃ አለ፡፡ ኑዛዜው ውል ክፍል ውስጥ በሥራ ቀን ሁለት ምስክሮች ባሉበት የተደረገና ሟችና ምስክሮች የፈረሙበትና በውል ክፍል የሚመለከተው ባለሥልጣን ባለበት የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ ለፍትሐሔር ሕግ ቁጥር 882 የተዛባ የሕግ ትርጉም በመስጠት ኑዛዜው ዋጋ የለውም ተብሎ መወሰኑ የሟችን የኑዛዜ ቃል ዋጋ የሚያሣጣና የህፃኑን መብት ሚጐዳ

በመሆኑ የሕግ ትርጉም ስህተቱ በሰበር ታርሞ ኑዛዜው ዋጋ አለው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል በሥርም ሆነ በሰበር ደረጃ ተከራካሪ የሆነ ተጠሪ የለም፡፡

አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሣኔና አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባነሽ መስከረም 27 ቀን 2001 ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው ያደረጉት ኑዛዜ በሁለት ምስክሮች እና በውልና ማስረጃ ሰራተኛ ፊት የተደረገና ወዲያውኑ ሟችና ምስክሮች የፈረሙበትና የውልና ማስረጃ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ትክክለኛነትን በማረጋገጥ በጽ/ቤቱ ማህተም በማተምና በፊርማው በማረጋገጥ ያደረጉት መሆኑን በሥር ከቀረበው ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 ድንጋጌ አንፃር መመዘን ያስፈልጋል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 "በግልጽ የሚደረገው ኑዛዜ ከምስክሮቹ መካከል አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜውም የተደረገው ይህ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ሥራቸውን በሚያካሄድበት ክፍል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ለኑዛዜው ዋጋ ለማግኘት ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ ናቸው"

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይህ ድንጋጌ ውል አዋዋይ ባለሥልጣኑ ስሙ በምስክርነት መገለጽ ያለበት መሆኑን እንደሚያስገድድ ኑዛዜው የተደረገው በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ቢሆንም ባለሥልጣኑ በምስክሮች ስም ዝርዝር ስሙ ካልተገለፀ የሕጉን ፎርም ኑዛዜው አያሟላም ኑዛዜው ህጋዊ ውጤት አይኖረውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ አተረጓጐም የህጉን መንስፌና አላማ የሚያሣካ ውጤታማ አተረጓጐም አይደለም፡፡ በቀረበው የኑዛዜ ማስረጃ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ያለው ባለሥልጣን ፊት የተደረገ፣ኑዛዜው ከተነበበ በኂላ ሁለቱ ምስክሮችና ሟች እንደፈረሙበት ይህ ሁሉ ተግባር በፊቱ ሲከናወን ጠቅላላ ሂደቱን የተከታተለው ውል ለማዋዋል ሥልጣን ያለው ባለሥልጣን ሂደቱ በአግባቡ የተፈፀመ መሆኑን በፊርማው በማረጋገጥና ማህተም በመምታትና ቁጥር በመስጠት አንድ ኮፒ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በማስቀረት ቀሪውን ለሟች እንደሰጠ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይህ መስፈርት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን ፎርም የሚያሟላና ህጉ ኑዛዜው የሟች እርግጠኛ የመጨረሻ ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ የደነገገውን መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ ስለዚህ አጠቃላይ ኑዛዜው የተደረገው ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው ባለሥልጣን ፊት መደረጉን በማረጋገጥ በመሥሪያ ቤቱ ማህተምና ፊርማ የተረጋገጠ ከሆነ የባለሥልጣኑ ስም በምስክሮች ፊት ስም ዝርዝር ውስጥ መጠቀሱ የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የባለሥልጣኑ ስም መገለጽ የሚያስፈልገው ከእሱ ውጭ ሌላ አንድ ምስክር ብቻ ከኖረ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ውል አዋዋይ ባለሥልጣኑ ውጭ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ያሉ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የሰጠው ትርጉም የሕጉን መንፈስና አጠቃላይ ግብ መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ ደስታ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞላ ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟላና ሕጋዊ ውጤት ያለው ኑዛዜ ነው ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ